የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 41
ADDIS ABABA 17th June, 2013

**ማውጫ**

**CONTENTS**

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፩/፪ሺ፭ ዓ.ም**

**የባህር አካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጣው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን (ማርፖል 73/78) ማፅደቂያ አዋጅ ... ..........ገጽ ፯ሺ፰፻፹**

**Proclamation No. 791/2013**

**International Convention for the Prevention of Pollution from Ships (MARPOL 73/78) Ratification Proclamation ............ Page 6880**

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፩/፪ሺ፭

**<u>የባህር አካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጣውን ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን (ማርፖል 73/78) ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ዓለም አቀፍ የባሕር ድርጅት እ.አ.አ. ኖቬምበር ፪ ቀን ፲፱፻፸፫ የባህር አካባቢ ብክለትን ለመከላከል ያወጣው ኮንቬንሽን እና እ.አ.አ. ፲፱፻፸፰ ኮንቬንሽኑ የተሻሻለበት ፕሮቶኮል (ማርፖል 73/78) እ.አ.አ ከኦክቶበር ፪ ቀን ፲፱፻፹፫ ጀምሮ ተፈፃሚ የተደረገ በመሆኑ፤

ይህንኑ ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የባህር አካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጣው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን (ማርፖል 73/78) ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፩/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 791/2013

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE INTERNATIONAL CONVENTION FOR THE PREVENTION OF POLLUTION FROM SHIPS (MARPOL 73/78)</u>**

WHEREAS, the International Maritime Organization adopted the International Convention for the Prevention of Pollution from Ships on the 2nd of November 1973 and the Protocol thereto in 1978 (MARPOL 73/78) which entered into force as of the 2nd of October 1983;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Convention at its session held on the 6th day of June, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "International Convention for the Prevention of Pollution from Ships (MARPOL 73/78) Ratification Proclamation No. 791/2013".

| ያንዱ ዋጋ Unit Price | 2.30. |
| --- | --- |

**፪. <u>የኮንቬንሽኑ መፅደቅ</u>**

የባህር አካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጣው አለም አቀፍ ስምምነት (ማርፖል 73/78) በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የትራንስፖርት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The International Convention for the Prevention of Pollution from Ships (MARPOL 73/78) is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Transport</u>**

The Ministry of Transport is hereby empowered to undertake, in cooperation with the concerned governmental organs, all acts necessary for the implementation of the Convention.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of June, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ